# ክልል አቀፍ የፀረ-ሙስና ጥምረት እና በየደረጃው

# የሚመሰረቱ ጥምረቶች ቻርተር ተግባራዊ ለማድረግ የወጣ

# የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 01/2004

መስከረም 2004
ሀዋሳ

# መግቢያ

ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተግባራት በየተቋማቱ ተደራሽ ሆነው የተጀመረው የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ በሙስናና ብልሹ አሰራር እንዳይደናቀፍ በማድረግ ሕብረተሰቡ የልማትና የመልካም አስተዳደር ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል በክልላችን የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች፣ የፀረ-ሙስና ንቅናቄ መድረኮች እና ጥምረቶች ስለሚደራጁበትና ስለሚሰሩበት ሁኔታ ለመወሰን በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በወጣው ደንብ ቁጥር 84/2003 ዓ.ም በመደንገጉ፣

በክልሉ የፀረ-ሙስና ጥምረት ቻርተር አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 6 የጥምረቱ ሥራ አስፈፃሚ ቻርተሩን መሰረት ያደረጉ ዝርዝር መመሪያዎችን በማውጣት ሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ተግባርና ሀላፊነት እንዳለው እንዲሁም በየአስተዳደር እርከኑ የፀረ-ሙስና ጥምረት መቋቋም እንዳለበት በቻርተሩ አንቀጽ 27 በመደንገጉ፣

በጥምረቱ ቻርተር ያልተሸፈኑና ያልተብራሩ ዝርዝር ጉዳዮች ተብራርተው የጥምረቱ አባል ተቋማት የተጣለባቸውን ተግባርና ሃላፊነት በአግባቡ እንዲያከናውኑ በመመሪያ ማስደገፍ በማስፈለጉ፣ የጥምረቱ የስብሰባ ሥርዓትና ሌሎች ጉዳዮች እንዲሁም የሪፖርት አቀራረብ በሴክሬታሪያቱ ተዘጋጅቶ በሥራ አስፈፃሚ በሚፀድቅ መመሪያ እንደሚወሰን በጥምረቱ ማቋቋሚያ ቻርተር አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አንቀጽ 31 ላይ እንደቅደምተከተላቸው የተመለከተ በመሆኑ፣ ጥምረቱ በአባልነት ለመቀጠል የማያስችል ጥፋት የፈጸመን አባል ከአባልነት የሚያሰናብትበት ሁኔታ በመመሪያ እንደሚወሰን በቻርተሩ አንቀጽ 28 በመደንገጉ፣ ክልላዊ የፀረ-ሙስና ጥምረት የመሰረቱ አደረጃጀቶች ጥምረቱን የመሰረቱበት ምክንያት በፀረ-ሙስና ትግሉ ውስጥ የየራሳቸውን አስተዋጽኦ በጋራና በተናጠል ለማበርከት በመሆኑ፣ ሁሉም የጥምረቱ አባል ተቋማት ለፀረ-ሙስና ትግሉ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ በእኩል ደረጃ ሊገኝ ስለማይችል የላቀ አርአያነት ያለው አስተዋጽኦ ያደረጉና ጥሩ ውጤት ያስገኙ አካላት የሚበረታቱበት ሁኔታ እንዲመቻች በቻርተሩ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 7 የተመለከተ በመሆኑ፣

ይህ መመሪያ በጥምረቱ መመስረቻ ቻርተር አንቀጽ 33 መሠረት በጥምረቱ ሥራ አስፈፃሚ ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### አንቀጽ 1-<u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ ‹‹ክልል አቀፍ የፀረ-ሙስና ጥምረት እና በየደረጃው የሚመሰረቱ ጥምረቶች ቻርተር ተግባራዊ ለማድረግ የወጣ የአፈፃጸም መመሪያ ቁጥር 01/2004›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 2 <u>ትርጓሜ</u>

**የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-**

1. ‹‹**ክልል**›› ማለት የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ነው፡፡
2. ‹‹**ጥምረት/ጥምረቱ**›› ማለት ሙስናን በተባበረ ሃይል በጋራ ለመታገል ከመንግሥት፣ ከመገናኛ ብዙሃን፣ ከግሉ ዘርፍና ከሲቪል ማህበረሰብ የተወጣጡ አካላት በፈቃደኝነት የመሠረቱት ክልል አቀፍ የፀረ-ሙስና ጥምረት እና በዚህ መመሪያ መሠረት በየደረጃው ባሉ የአስተዳደር እርከኖች የሚመሰረቱ የፀረ-ሙስና ጥምረቶች ናቸው፡፡
3. ‹‹**ቻርተር/ቻርተሩ**›› ማለት ክልል አቀፍ የፀረ-ሙስና ጥምረት መመስረቻ ቻርተር ነው፡፡
4. ‹‹**መመሪያ**›› ማለት በጥምረቱ መመስረቻ ቻርተር ያልተካተቱና በዝርዝር ያልተብራሩ ጉዳዮችን በማብራራት ቻርተሩን ተግባራዊ ለማድረግ የተዘጋጀ የአደረጃጀትና የአሠራር መመሪያ ነው፡፡
5. ‹‹**ጠቅላላ ጉባኤ**›› ማለት በቻርተሩ መሠረት የጥምረቱ አባላት በሙሉ የሚወከሉበት መደበኛ ወይም አስቸኳይ ስብሰባ ነው፡፡
6. ‹‹**ሥራ አስፈፃሚ**›› ማለት በየደረጃው በሚቋቋም የፀረ ሙስና ጥምረት ጠቅላላ ጉባኤ የሚሰየም የፀረ ሙስና ጥምረት የበላይ አመራር ማለት ነው፡፡
7. ‹‹**ሴክረታሪያት/ሴክሬታሪያቱ**›› ማለት በቻርተሩ መሠረት የክልሉ የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ነው፡፡

8. **‹‹መደበኛ ስብሰባ››** ማለት በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሠረት በጥምረቱ ጠቅላላ ጉባኤ በዓመት አንድ ጊዜ፣በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በዓመት አራት ጊዜ የሚካሄድ ስብሰባ ነው።

9. **‹‹አስቸኳይ ስብሰባ››** ማለት በሁለት መደበኛ ስብሰባዎች መካከል ውሳኔ የሚያስፈልገው ጉዳይ ሲያጋጥም የሚካሄድ ስብሰባ ነው።

10. **‹‹ኮሚሽን››** ማለት የክልሉ የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ነው።

11. **‹‹የሥራ አስፈፃሚ ሰብሳቢ››** ማለት በቻርተሩ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት ከክልሉ ምክትል ርዕሳነ መስተዳድሮች መካከል የሚሰየም የሥራ አስፈፃሚ ሰብሳቢ ነው።

12. **‹‹የጥምረቱ ሰብሳቢ››** ማለት የክልል አቀፍ የፀረ-ሙስና ጥምረት ጠቅላላ ጉባኤ ሰብሳቢ ነው።

13. **"ፀሐፊ"** ማለት በዞን፣ በልዩ ወረዳ፣ በወረዳና በከተማ አስተዳደር ደረጃ የሚቋቋመውን የፀረ ሙስና ጥምረት በፀሐፊነት የሚያገለግል የሥነ ምግባር ኦፊሰር ነው።

14. **‹‹የጥምረት አባላት››** ማለት በጥምረቱ መመስረቻ ቻርተር በመሥራችነት የተጠቀሱትን እና በሥራ አስፈፃሚ ወይም በጥምረቱ ውሳኔ አባል እንዲሆኑ የተደረጉትን ያካትታል።

15. **‹‹ኮሚቴ››** ማለት በፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ የተሻለ አስተዋጽኦ ላደረጉ አካላት እውቅና ለመስጠት ተግባር በሥራ አስፈፃሚ የሚሰየም ኮሚቴ ነው።

16. **‹‹የሥነ-ምግባር ኦፊሰር››** ማለት በየደረጃው የሚቋቋመው የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኦፊሰር ሆኖ የሚያገለግል ሠራተኛ ነው።

## አንቀጽ 3- <u>የፆታ አገላለጽ</u>

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴት ፆታንም ይጨምራል።

## አንቀጽ 4 <u>የአፈፃጸም ወሰን</u>

ይህ መመሪያ የጥምረቱ አባላት በቻርተሩ ላይ የተቀመጡ ዓላማዎችንና ተግባራትን ለማሳካት በሚያደርጉት የጋራ እንቅስቃሴ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 5 <u>መርህ</u>

1. የዚህ መመሪያ አፈፃጸም የአባላትን በህግ የተሰጠውን ተቋማዊ ነፃነት ባከበረ ሁኔታ ነው፡፡
2. የጥምረቱ አባላት መመሪያውን የማክበርና የማስፈጸም ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው
3. የጥምረቱ አባላት ተግባራቸውን የሚያከናውኑት በቻርተሩና በዚህ መመሪያ መሠረት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 6 <u>የመመሪያው ዓላማዎች</u>

<u>መመሪያው ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩ ዋና እና ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል</u>

### 6.1 <u>ዋና ዓላማ</u>

በየደረጃው የፀረ ሙስና ጥምረቶችን በማደራጀትና አሠራራቸውን ግልፅ በማድረግ የፀረ-ሙስና ትግሉን ተቋማዊ እና ሕዝባዊ መሠረት በማስያዝ የተጀመረው የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በሙስና እንዳይደናቀፍ፣ ሙስና የክልሉ ማህበረ ኢኮኖሚያዊና መልካም አስተዳደር እንቅፋት የማይሆንበት ደረጃ ለማድረስና ሙስናን የማይሸከም ኅብረተሰብ መፍጠር ነው፡፡

### 6.2 <u>ዝርዝር ዓላማዎች</u>

ሀ. የፀረ-ሙስና ጥምረቶች አደረጃጀትና አሠራር ለማጠናከር፣

ለ. ጥምረቶቹ ተልዕኮአቸውን በብቃት ለመፈፀም የሚያስችል የአሠራር ግልፅነት ለመፍጠር፣

ሐ. የጥምረቱ ሰብሰባዎች በቅድመ ዝግጅት ተቀናብረው የተቀላጠፉ እና ውጤታማ እንዲሆኑና በተሳታፊዎች ትኩረት እንዲሰጣቸው ለማድረግ፣

መ. የጥመረቱ አባላት መብትና ግዴታቸውን እንዲያውቁ ለማስቻል፣

ሠ. የጥምረቱን አባላት በዲስፒሊን እንዲመሩ በማድረግ የጥምረቱን ቀጣይነት ለማረጋገጥ፣

ረ. በፀረ-ሙስና ትግሉ የተሻለ ተሳትፎ ያደረጉ አካላትንና ግለሰቦችን በማበረታታት የመልካም ሥነ-ምግባር እሴቶች እንዲስፋፉ ለማድረግ፣

ሰ. የጥምረቱ በጀትና ፋይናንስ በህጋዊ መልኩ ፣ግልጸኝነትና ተጠያቂነት ባለው አግባብ እንዲመራ ለማድረግ፣

ሸ. በየደረጃው ያሉ የጥምረቱ አባላት የሚኖራቸውን የግኑኝነት ሁኔታ ለመወሰን፣

## ክፍል ሁለት

## በየደረጃው የፀረ-ሙስና ጥምረት ስለ መመስረት

### አንቀጽ 7 የጥምረቱ መመስረት

1. የክልሉ የፀረ-ሙስና ጥምረት ቻርተር እና ይህ መመሪያ መሠረት ተደርጐ በዞኖች፣ በልዩ ወረዳዎች፣ በወረዳዎችና በከተማ አስተዳደሮች የፀረ-ሙስና ጥምረቶች ይመሰረታሉ፡፡
2. ጥምረቶቹ የሚመሰረቱት በየአስተዳደር እርከኑ የሚመለከታቸው አካላት የክልሉን የፀረ-ሙስና ጥምረት ቻርተር መሠረት አድርገው በሚያዘጋጁት የየራሳቸው መመሥረቻ ቻርተር ላይ ውይይት አድርጐ በማጽደቅ ይሆናል፡፡
3. በየደረጃው ያሉ አካላት የፀረ-ሙስና ጥምረት ለማቋቋም በሚያደርጉት ጥረት ኮሚሽኑ አስፈላጊውን የቴክኒክና የምክር ድጋፍ ይሰጣል፡፡

### አንቀጽ 8 የጥምረቱ አቋም

1. በዞኖች፣ በልዩ ወረዳዎች፣ ወረዳዎችና በከተማ አስተዳደሮች የሚመሰረተው ጥምረት የሚከተለው አቋም ይኖረዋል፡፡

   ሀ. ጠቅላላ ጉባኤ

   ለ. የጠቅላላ ጉባኤ ሰብሰቢ

   ሐ. የጠቅላላ ጉባኤ ም/ሰብሳቢ

   መ. ሥራ አስፈፃሚ

   ሠ. የሥራ አስፈፃሚ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢና ፀሐፊ

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 /ሀ-ሠ የተዘረዘሩ አካላት ተግባርና ኃላፊነት በክልሉ የፀረ-ሙስና ጥምረት ቻርተር አንቀጽ 16 /1-8፣10፣ አንቀጽ 17 /1-8፣ አንቀጽ 18 /1-3፣ አንቀጽ 20 /1-5፣ አንቀጽ 21/1-8፣ አንቀጽ 22/1-3፣ አንቀጽ 23/1-4 የተዘረዘሩ ተግባራትና ሃላፊነቶች ይኖራቸዋል

## አንቀጽ 9 ስለ ጥምረቱ አባላት አወካከል

1. በየደረጃው የሚቋቋሙው የፀረ-ሙስና ጥምረት መሥራች አባላት አወካከል የየአስተደደር እርከኑን ተጨባጭ ሁኔታ መሠረት ባደረገ መልኩ የክልሉን የፀረ-ሙስና ጥምረት ቻርተር ተከትሎ ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በየደረጃው የሚገኙትን አደረጃጀቶችና የየአከባቢያቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት የጥምረቱን አባላት ቁጥር ሊወስኑ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ 10 የጥምረቱ ፀሐፊ

በየደረጃው ባሉት በአስተዳደር/በካንቲባ ጽ/ቤቶች ሥር የሚቋቋመው የሥነ-ምግባር ኦፊሰር ከሥነ-ምግባር ኦፊሰርነት ተግባሩ በተጨማሪ የየጥምረቱ ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል፡፡

## አንቀጽ 11 የጥምረቱ ፀሐፊ ተግባርና ኃላፊነት

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 1፣2፣3፣4፣5 እና 6 የተዘረዘሩ ተግባራትና ኃላፊነት ይኖሩታል፡፡

## አንቀጽ12 የጥምረቱ ሥራ አስፈፃሚዎች የሥራ ዘመን

በየደረጃው የሚመሰረተው የፀረ-ሙስና ጥምረት ሥራ አስፈፃሚዎች የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል፡፡

## ??? ???

## ?? ???? ???? ????? ? ?? ???

## አንቀጽ 13 የጥምረቱ መደበኛ  ስብሰባዎች

1. ጥምረቱ የጠቅላላ ጉባኤ፣ የሥራ አስፈፃሚ እና የኮሚቴ መደበኛና አስቸኳይ ስብሳባዎች ይኖሩታል፡፡
2. ጠቅላላ ጉባኤው አስቸኳይ ስብሰባ የሚያስጠራ ጉዳይ ካላጋጠመው በስተቀር በዓመት ውስጥ አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡
3. ሥራ አስፈፃሚው አስቸኳይ ስብሰባ የሚያስጠራ ጉዳይ ካላጋጠመው በስተቀር በዓመት ውስጥ 4 መደበኛ  ስብሰባዎች ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ 14 የጥምረቱ አስቸኳይ ስብሰባዎች

1. የጥምረቱ ሰብሳቢ የጠቅላላ ጉባኤ እና የሥራ አስፈፃሚ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡
2. 1/3ኛ የሚሆኑ የሥራ አስፈፃሚ ወይም የጠቅላላ ጉባኤ አባላት እንደቅደምተከተሉ የሥራ አስፈፃሚ ወይም ጠቅላላ ጉባኤ አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡
3. የጥምረቱ ሴክሬታሪያት የሥራ አስፈፃሚ ወይም የጠቅላላ ጉባኤ አስቸኳይ ስብሰባዎች ጥሪ ያስተላልፋል፡፡
4. የጥምረቱ ሰብሳቢ አስቸኳይ ስብሰባ የመጥራት መብት ባለው አካል ሲጠየቅ የመጥራት ግዴታ አለበት ፡፡

## አንቀጽ 15 የጥምረቱ አባላት መብቶች

በክልሉ የፀረ-ሙስና ጥምረት ቻርተር አንቀጽ 10 እንደተመለከተው እያንዳንዱ የጥምረቱ አባል የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

1. በጥምረቱ ስብሳባዎችና በተመረጠባቸው ቦታዎች ሀሳቡን በነፃነት የማንሸራሸርና በንቃት የመሳተፍ፣
2. ውይይት እንዲደረግበት የሚፈልገውን ጉዳይ በጥምረቱ አሰራር መሰረት አጀንዳ የማስያዝ፣
3. ውሳኔ በሚጠይቁ ጉዳዮች ላይ ድምጽ የመስጠት፣
4. ለጥምረቱ ሥራ የመምረጥና የመመረጥ፣

## አንቀጽ 16 የጥምረቱ አባላት ግዴታዎች

እያንዳንዱ የጥምረቱ አባል የሚከተለው ግዴታ ይኖረዋል፡፡

1. በጥምረቱ ስብሰባዎች የመገኘት፣
2. የተስማማበትን የጥምረቱን ውሳኔ የመተግበር፣
3. ለሠራተኞቹ፣ ለአባላቱና እንደ ሁኔታውም ለኅብረተሰቡ የሥነ ምግባር እና የፀረ ሙስና ትምህርት የመስጠት ወይም እንዲሰጥ የማድረግ ወይም የመደገፍ፣
4. ውስጣዊ አሠራሩን ቀልጣፋ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው እንዲሆን የማድረግ፣
5. ስላከናወናቸው መልካም ሥነ ምግባርን የማስፋፋትና ሙስናን የመዋጋት ተግባራት በጥምረቱ አሠራር መሠረት ሪፖርት የማድረግ፣

6. የጥምረቱ አባላት በየደረጃው በሚጠሩባቸው ስብሰባዎች ሁሉ አባሎቻቸውን የመወከል ግዴታ አለባቸው
7. ከየተቋማቱ በየደረጃው በሚካሄዱ ስብሰባዎች እንዲሳተፍ የተወከለ ተሳታፊ የስብሰባ ሰዓት ማክበር አለበት

**አንቀጽ 17 <u>ምልአተ ጉባኤና የድምጽ አሠጣጥ ሥነ-ሥርዓት</u>**

1. ማንኛውም የጥምረቱ ስብሰባ ከአባላቱ ከግማሽ በላይ /50+1/ ሲገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡
2. በማንኛውም የጥምረቱ ስብሰባ ውሳኔ ሲተላለፍ አንድ አባል አንድ ድምጽ ይኖረዋል፡፡
3. በማንኛውም የጥምረቱ ስብሰባ ውሳኔ የሚተላለፈው ከግማሽ በላይ /50+1/ ተሰብሳቢ ውሳኔውን ሲደግፈው ነው፡፡
4. ድምጽ እኩል በእኩል ሲሆን ሰብሳቢው የደገፈው የውሳኔ ሃሳብ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
5. ማንኛውም የጥምረቱ ውሳኔ ከሀገሪቱ ህጎችና የጥምረቱ ቻርተር ጋር መጣጣም ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ 18 <u>ስለስብሰባ አጠራር</u>**

1. የጥምረቱ ሴክሬታሪያት/ፀሐፊ ከሰብሳቢው ጋር በመመካከር የስብሰባውን አጀንዳ ያዘጋጃል፣ የስብሰባውንም ቦታ ይወስናል፡፡
2. ሰብሳቢው የጠቅላላ ጉባኤ መደበኛ ስብሰባ ጥሪ በደብዳቤ ከ20 ቀናት በፊት ለተሳታፊዎች እንዲደርስ ያደርጋል፡፡
3. የሥራ አስፈፃሚ መደበኛ ስብሰባ ጥሪ ደብዳቤ ከ5 ቀናት በፊት በሥራ አስፈፃሚው ሰብሳቢ ወይም በሴክሬታሪያቱ/ፀሐፊ ለተሳታፊዎች ይተላለፋል፡፡
4. የሥራ አስፈፃሚ አስቸኳይ ስብሰባ ከ3 ቀናት በፊት፣ የጠቅላላ ጉባኤ አስቸኳይ ስብሰባ ከ10 ቀናት በፊት ጥሪ ይተላለፋል፡፡
5. ኮሚቴዎች ቋሚ የስብሰባ ቀን ሊወሰኑ ወይም በስብሰባቸው መጨረሻ የቀጣዩን የስብሰባ ቀን ሊወስኑ ይችላሉ፡፡
6. ማንኛውም የስብሰባ ጥሪ የስብሰባውን አጀንዳ፣ የስብሰባውን ቦታና ስብሰባው የሚጀመርበትን ሰዓት የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## ስለ ዕቅድና ሪፖርት አቀራረብ

### <u>አንቀጽ 19 ስለ ዕቅድና ሪፖርት አላላክ</u>

1. እያንዳንዱ የክልል የፀረ ሙስና ጥምረት ወይም በየደረጃው የሚያቋቋሙ ጥምረቶች አባል ተቋማት በዓመት አንድ ጊዜ ዕቅዳቸውን አዘጋጅተው እንደቅደምተከተሉ ለጥምረቱ ሴክሬታሪያት ወይም ለየጥምረቶቻቸው ፀሐፊ ማቅረብ ይኖርባቸዋል
2. እያንዳንዱ የክልል የፀረ-ሙስና ጥምረት ወይም በየደረጃው የሚቋቋሙ ጥምረቶች አባል ተቋማት በየ3 ወሩ፣ በየ6 ወሩ እና በዓመት የእቅድ ክንውን ሪፖርታቸውን እንደቅደምተከተሉ ለጥምረቱ ሴክረታሪያት ወይም ለየጥምረቶቻቸው ፀሐፊ መላክ አለባቸው
3. በየደረጃው የተቋቋመው ጥምረት በደረጃ ከፍ ብሎ ለተመሰረተው ጥምረት ሴክረታሪያት ወይም የጥምረቱ ፀሐፊ አመታዊ ዕቅድ አዘጋጅቶ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡
4. በየደረጃው የተቋቋመው ጥምረት በየ3 ወሩ፣ በ6 ወር እና በዓመት የዕቅድ ክንውን ሪፖርት በአደረጃጀት ከፍ ብሎ ለተመሰረተው ጥምረት ሴክሬታሪያት ወይም የጥምረቱ ፀሐፊ መላክ አለባቸው

### አንቀጽ 20 <u>ስለ ዕቅድና ሪፖርት ይዘት</u>

1. የላኪው ሥም፣ ማህተም እና አግባብ ያለው ኃላፊ ፊርማ፣
2. ዕቅድና ሪፖርቱ የሚሸፍነው ጊዜ እና የተላከበትን ቀን ያሟላ መሆን አለበት፡፡
3. እቅድና ክንውኑ ተነፃጽሮ መቅረብ አለበት

### አንቀጽ 21 <u>የዕቅድ ዝርዝር ይዘት</u>

**በአንቀጽ 20 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-**

1. እያንዳንዱ እቅድ በዓመትና በየሩብ በጀት ዓመቱ የሚከናወኑትን ተግባራት የሚያሳይ መሆን አለበት፡፡
2. ከመንግስት ተቋማት ውጭ ባሉ አባል ተቋማት የሚዘጋጅ ዕቅድ የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ትምህርት የማስፋፋት፣ ሙስና የመከላከል እና በበጀት ዓመቱ እንዲከናወኑ የተያዙ ሌሎች ተግባራትን /ካሉ/ማካተት አለበት፡፡

3. በመንግስት ተቋማት የሚቀርብ እያንዳንዱ ዕቅድ የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ትምህርት የማስፋፋት፣ ሙስናን የመካላከል /የአሰራር ሥርዓት ጥናት፣ የሥነ-ምግባር ደንብ ዝግጅት፣ የሀብት ምዝገባ እና የተፈጸሙ ከሥነ-ምግባር ውጪ የሆኑ ችግሮችን ለይቶ በማጣራት አስተዳደራዊ እርምጃ የመውሰድ ወይም ተቋማት ከእነሱ አቅም በላይ የሆነውን ወደ ኮሚሽኑ ሪፖርት የማድረግ እና የፍትህ አካላት የሙስና ተግባራትን የማጣራትና የመክሰስ ተግባራትን ማካተት አለበት፡፡

## አንቀጽ 22 <u>የዕቅድ ክንውን ሪፖርት ዝርዝር ይዘት</u>

**በአንቀጽ 21 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ**

1. የጥምረቱ አባል ተቋማት በየሩብ ዓመቱ፣ በ6 ወር እና በየአመቱ የክንውን ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው፡፡
2. ከመንግስት ተቋማት ውጭ ባሉ አባል ተቋማት የሚቀርብ ማንኛውም ሪፖርት የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ትምህርቶችን በማስፋፋት፣ የሙስና ወንጀልን በመከላከል እና ሌሎች በበጀት ዓመቱ የታቀዱ ተግባራት /ካሉ/ክንውንን ማካተት አለበት፡፡
3. በክልሉ መንግስት ተቋማት የሚቀርብ ማንኛውም ሪፖርት የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ትምህርትን በማስፋፋት፣ የሙስና ወንጀልን መከላከልና ከሥነ-ምግባር ውጪ የሆኑ ችግሮችን እና የሙስና ወንጀሎችን በማጣራት አስተዳደራዊ እርምጃ የመውሰድ ወይም ለሚመለከተው አካል የማስተላለፍ ተግባራትን ማካተት አለበት፡፡
4. በሁሉም አካላት የሚቀርቡ ሪፖርቶች በዕቅዱ መሠረት የተከናወኑና ያልተከናወኑ፣ ያልተከናወነበት ምክንያት እንዲሁም ከዕቅድ ወጪ የተከናወኑ እና በዕቅድ ክንውን ወቅት የታዩ ምርጥ ተሞክሮዎች ማካተት አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 23 <u>ስለሚቀርበው ዕቅድና ሪፖርት ግልጽነትና ተአማኒነት</u>

1. የሚቀርበው ሪፖርት ግልጽና ተአማኒነት ያለው መሆን አለበት፣ ቢቻል ከደጋፊ ማስረጃ (ፎቶ ግራፍ፣ ቪዲዮ ካሴት እና የመሳሰሉት) ጋር መቅረብ ይኖርበታል፡፡
2. አንድ አባል ተቋም የሚልከው ሪፖርት ካቀደው ዕቅድ ጋር ተመሳሳይና የማይጣረስ መሆን ይኖርበታል፡፡
3. ከዕቅድ ውጪ የተከናወኑ ተግባራት ካሉ ይኸው ተጠቅሶ ሪፖርት ይደረጋል፡፡

## አንቀጽ 24 <u>በሴክሬታሪያቱ/በፀሐፊ ስለሚዘጋጁ ዕቅድና ሪፖርቶች</u>

1. የጥምረቱ የ5 ዓመት መሪ ዕቅድ ተዘጋጅቶ በሥራ አስፈፃሚው ከተገመገመ በኋላ ለጉባኤው ቀርቦ ይፀድቃል፣
2. የሥራ አሰፈፃሚው ዓመታዊ ዕቅድ ተዘጋጅቶ በስብሰቢው አማካኝነት ለሥራ አስፈጻሚው ቀርቦ ይፀድቃል፣
3. ከአባል ተቋማት ስለአከናወኗቸው ተግባራት በአንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት ሪፖርት በመቀበል ያጠናቅራል፣ የሠነዶቹን ትክክለኛነት ያረጋግጣል፣ ግብረመልስ ይሰጣል፣ የተጠቃለለ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፣

## አንቀጽ 25 <u>የዕቅድ ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ</u>

1. ሴክሬታሪያቱ ይህንን መመሪያ መሠረት በማድረግ አባላት የፀረ-ሙስና ትግላቸውን የሚመሩበት ዕቅድና የክንውን ሪፖርት የሚያቀርቡበት ቅጽ አዘጋጅቶ እንዲደርሳቸው ያደርጋል።
2. ሴክሬታሪያቱ ለሁሉም አባላት ተመሳሳይ ወይም የተለያዩ የዕቅድና የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጾችን ሊያዘጋጅ ይችላል።
3. ሴክሬታሪያቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ቅጾቹን ሊያሻሽላቸው ይችላል።
4. የጥምረቱ አባል ተቋማት በሴክሬታሪያቱ ተዘጋጅቶ በተላከላቸው ቅጽ መሠረት ዕቅድና ሪፓርቶቻቸውን አዘጋጅተው ለየጥምረታቸው በወቅቱ ማቅረብ አለባቸው።

## ክፍል አምስት

## ከጥምረቱ አባልነት ስለ ማሰናበት

### አንቀጽ 26 ስንብት

1. የጥምረቱ ጠቅላላ ጉባኤ በአባልነት ለመቀጠል የማያስችል ጥፋት የፈፀመን አካል ከአባልነት ለማሰናበት ይችላል።
2. ፈቃድ ተሰጥቶት በሚሰራበት የሥራ መስክ ህገወጥ ተግባር በመፈጸሙ ሥልጣን ባለው አካል የታገደ የጥምረቱ አባል ከአባልነት ይሰናበታል።
3. በህገወጥ ተግባር ወይም በጥፋቱ ከኃላፊነቱ የተነሳ ኃላፊ ተቋሙን አይወክልም፣

### አንቀጽ 27 ከአባልነት የሚያሰናብቱ ሁኔታዎች

1. በተደጋጋሚ የተስማማበትን የጥምረቱን ውሳኔዎች ለመተግበር ፍቃደኛ አለመሆን፣
2. ምክንያቱን ሳያሳውቅ በተደጋጋሚ በጥምረቱ የተለያዩ ሰብሰባዎችና ጉባኤዎች አለመገኘት ወይም የሥልጠና ኘሮግራሞች አለመሳተፍ፣
3. የጥምረቱን የመመስረቻ ቻርተርና የአሰራር መመሪያ በተደጋጋሚና ሆነ ብሎ አለማክበር፣
4. አሳማኝ ምክንያት ሳይኖረው በበጀት ዓመቱ ውስጥ በጥምረቱ አሠራር መሠረት ዕቅድ አውጥቶ ያለመንቀሳቀስና የክንውን ሪፖርት ያለማቅረብ፣

### አንቀጽ 28 ከስንብት በፊት ስለሚኖሩ ሂደቶች

1. በመጀመሪያ ጊዜ የቀረ አባል የቀረበትን ምክንያት ለሥራ አስፈጻሚ ሰብባቢ በመግለጽ ሰብሳቢው ውሣኔ ይሰጥበታል፣
2. ለሁለተኛ ጊዜ ከቀረ ለወከለው ተቋም በጥምረቱ ሥራ አስፈጻሚ ሰብሳቢ ማስጠንቀቂያ ይጻፍበታል፣
3. ለሦስተኛ ጊዜ የቀረ አባል የቀረበትን ምክንያት ለሥራ አስፈጻሚ ሰብባቢ በመግለጽ የሥራ አስፈጻሚ ሰብሳቢ ለሥራ አስፈጻሚ አባላት በማቅረብ ውሣኔ እንዲስጥ ያደርጋል፣
4. ለአራተኛ ጊዜ ከቀረ የጥምረቱ ሥራ አስፈጻሚ ለጥምረቱ ጠቅላላ ጉባኤ ሰብሳቢ ያሳውቃል፣
5. በመጨረሻ ለጥምረቱ ጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ ይወስናል፣

## አንቀጽ 29 <u>በራስ ፈቃድ ከአባልነት ስለ መልቀቅ</u>

1. በጥምረቱ አባልነት የሚያደርገው እንቅስቃሴ ተቋማዊ ነፃነቴን ይነካል ብሎ ያመነ አካል ተቋማዊ ነፃነቱን እንዴት እንደሚነካበት ለጥምረቱ ጉባኤ በማስረዳት ከአባልነት መልቀቅ ይችላል፡፡
2. በጥምረቱ አባልነት ለመቀጠል የማይፈልግ አካል ምክንያቱን ለጉባኤው አሳውቆ በራሱ ፈቃድ ከአባልነት መልቀቅ ይችላል፡፡
3. ማንኛውም አባል የመልቀቂያ ጥያቄውን ከነምክንያቱ በጽሑፍ ለጥምረቱ ሥራ አስፈፃሚ ማቅረብ አለበት፡፡
4. የስንብት ጥያቄው ለጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ ውሳኔ እስኪሰጥበት ድረስ ጥያቄ አቅራቢው አካል በአባልነቱ ይቀጥላል፡፡

## አንቀጽ 30 <u>የማሰናበት ስልጣን</u>

1. ከጥምረት አባልነት የማሰናበት ሥልጣን የጥምረቱ ጠቅላላ ጉባኤ ነው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው ቢኖርም የጥምረቱ ሥራ አስፈፃሚ ከአባልነት የመልቀቅ ጥያቄዎችን ተቀብሎ በመገምገም ለውሳኔ ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፡፡
3. የጥምረቱ ሰብሳቢ በጥምረቱ አባልነት ለመቀጠል የማያስችል ሁኔታ የሚታይበትን አባል ለሥራ አሰፈፃሚው ማቅረብ ይችላል፡፡
4. ከጥምረት አባልነት እንዲሰናበት በጠቅላላ ጉባኤ ያልተወሰነበት አባል በአባልነቱ እንዳለ ይቆጠራል፡፡

## አንቀጽ 31 <u>ስለተሰናበተ የጥምረቱ አባል</u>

1. ከጥምረቱ አባልነት የተሰናበተ አባል በጥምረቱ የሚፈለግበት የጋራ ንብረት /ቁሳቁስ በእጁ ካለ ለጥምረቱ ጠቅላላ ጉባኤ ሰብሰቢ ወይም ለስራ አስፈፃሚ ሰብሳቢ ወይም ለሴክሬታሪያቱ ያስረክባል፡፡
2. ከጥምረቱ አባልነት የተሰናበተ አባል በይቅርታ ወደ ጥምረቱ የመመለስ የአባልነት ጥያቄ ለጥምረቱ ጠቅላላ ጉባኤ ሰብሳቢ ወይም ለሥራ አስፈፃሚው ሊያቀርብ ይችላል፡፡

3. ጠቅላላው ጉባኤው የይቅርታ የአባልነት ጥያቄ ከተቀበለው ከአባልነት የተሰናበተው አካል እንደገና አባል ይሆናል፡፡
4. የመድረኩ ስራ አስፈፃሚ ከአባልነት የተሰናበተን አባል ከስንብት በኋላ ያለውን አቋም ገምግሞ ወደ አባልነት እንዲመለስ ሊጠይቀው ይችላል፡፡

**ክፍል ስድስት**

**በፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ አስተዋጽኦ ላደረጉ አካላት**

**ዕውቅና ስለመስጠት**

**አንቀጽ 32 <u>ዕውቅና ስለሚያገኙ አካላት</u>**

በበጀት አመቱ በመወዳደሪያ መስፈርቶች ተመዝነው የተሻለ እንቅስቃሴ ያደረጉ ተቋማት፣ አካላት፣ ግለሰቦች ተመርጠው ዕውቅና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

1. የክልልና በየደረጃው የሚደራጁ የፀረ-ሙስና ጥምረት አባል ተቋማት፣
2. የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች፣
3. የሴቶችና የወጣቶች የፀረ-ሙስና ንቅናቄ መድረኮች፣
4. በትምህርት ተቋማት የተቋቋሙ የሥነ-ምግባርና የሥነ-ዜጋ ክበባት፣
5. የሚዲያና የኪነ ጥበብ የጋራ መድረክ እና
6. የፍትህና አግባብነት ያላቸው አካላት የጋራ መድረክ፣
7. ግለሰቦች ናቸው ፡፡

**አንቀጽ 33 <u>የመምረጫ መስፈርት</u>**

የመምረጫ መስፈርቶች ግልጽ መረጃ የሚገኝላቸውና ሊለኩ የሚችሉ ጉዳዮችን ታሳቢ በማድረግ ከዚህ በታች በዕውቅና መስጫ ዘርፉ በሚቀርበው መሠረት ይፈጸማል፡፡

**አንቀጽ 34 <u>በፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ የተሻለ አስተዋጽኦ ያደረገ አካል</u>**

ይህ እውቅና መንግስት በቀየሰው የፀረ-ሙስና ትግል ስትራቴጂ ውስጥ የጐላ አፈፃጸም በማስመዝገብ አስተዋጽኦ ያደረጉ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 32 የተጠቀሱትን የሚያካትት ሆኖ

በመረጃ በተደገፈ የግምገማ ውጤት መሠረት ለውድድር ብቁ ከሆኑት ከ1ኛ-3ኛ ደረጃ የሚወጡት ዕውቅና ይሰጣቸዋል፡፡

## አንቀጽ 35 መስፈርት

| ተ.ቁ | መስፈርት | ክብደት በመቶኛ | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ትምህርትን ማስፋፋት | 15 | |
| 2 | የውስጥ አሰራሩ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው እንዲሆን የሥነ-ምግባር መመሪያ በማዘጋጀትና የሥነ-ምግባር መርሆች የዕለት ተዕለት ተግባር አካል እንዲሆን ማድረግ | 15 | |
| 3 | በፀረ-ሙስና ትግል አርአያነት እና ተጨባጨነት ያለው ተግባር መፈጸም | 15 | |
| 4 | ሌሎች የሥነ-ምግባር አውታሮች መደገፍና በቅንጅት መስራት | 15 | |
| 5 | የአሠራር ሥርዓት ማሻሻያ | 10 | |
| 6 | ለጥምረቱ በሚቀርበው ዕቅድና ሪፖርት | 10 | |
| 7 | በጋራ ጉባኤዎችና ሌሎች ስብሰባዎች ላይ መገኘትና ንቁ ተሳትፎ ማድረግ | 10 | |
| 8 | ሌሎች የጥምረቱ አባላት ተሳትፎዎች | 10 | |

1. የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ትምህርትን በማስፋፋት የተሻለ እንቅስቃሴ አድርጓል ተብሎ ዕውቅና የሚሰጠው በአንድ ዓመት እንዲፈፀም የተያዘውን እቅድ ሙሉ በሙሉ ወይም ከዚያ በላይ ማከናወኑ ሲረጋገጥና ይህ ክንውን ከሌሎች ጋር ተወዳድሮ የተሻለ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡
2. የውስጥ አሰራሩ ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለው እንዲሆን በማድረግ የሥነ-ምግባር መመሪያ በማዘጋጀትና የስነ-ምግባር መርሆች የዕለት ተዕለት ተግባር አካል እንዲሆን የተሰራው ሥራ ዕውቅና የሚሰጠው ብቃት ያለው ሰው ለዚህ ሥራ በወቅቱ ሲመደብና ሥራውን በተገቢዉ እንዲሰራ ሲያደረግ እንዲሁም ሊያሰራ የሚችል የሥነ-ምግባር ደንብ አዘጋጅቶ ሥራ ላይ ሲያውል ወይም የተዘጋጀው የሥነ-ምግባር መመሪያ ያለ መሆኑ ሲረጋገጥ እና ከሌሎች ጋር ሲወዳደር የተሻለ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡
3. በፀረ-ሙስና ትግል አርአያነትና ተጨባጭነት ያለው ተግባር መፈጸም እውቅና የሚሰጠው በተጨባጭ መረጃ ተመስርቶ የሙስና ተግባራትን በማጋለጥ ሲሆን ይህም ከሌሎች ጋር ተወዳድሮ የተሻለ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡

4. ሌሎች የሥነ-ምግባር አውታሮችን መደገፍና በቅንጅት መስራት እውቅና የሚሰጠዉ የፀረ-ሙስና ትግሉን ሕዝባዊ መሰረት ለማስያዝ በሕብረተሰቡ ውስጥ የፀረ-ሙስና ንቅናቄ በመፍጠር፣የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎችንና የፀረ-ሙስና ንቅናቄ መድረኮችን በመደገፍ ሲሆን ይህም ከሌሎች ጋር ተወዳድሮ የተሻለ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡
5. የአሰራር ሥርዓት ጥናት ማሻሻያ እዉቅና የሚሰጠው በየተቋሞቻቸው ውስጥ ለሙስና ብልሹ አሰራር የተጋለጡ አሰራሮችን በመለየት፣ ከመስሪያ ቤቱ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ጋር በመወያየት፣ ተቋማዊ ጥናት በማካሄድና በጥናቱ መሠረት ወደ ሥራ በመግባት ሲሆን ይህም ከሌሎች ጋር ተወዳድሮ የተሻለ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡
6. ለጥምረቱ የሚቀርበው ዕቅድና ሪፖርት የሚለካው የተሟላ ዕቅድና ሪፖርት በወቅቱ በማቅረብ ተወዳድሮ ከሌሎች የተሻለ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡
7. በጋራ ጉባኤዎችና ሌሎች በጥምረቱ በሚጠሩ ስብሰባዎች ላይ መገኘትና ንቁ ተሳትፎ የሚለካው እንዲያሳትፋቸው ከሚጠበቁ ሰዎች ባሳታፋቸው ሰዎች ብዛት፣ በወቅቱ እንዲገኙ በማድረግና በመድረክ በሚያሳዩት ተሳትፎና ስብሰባውን በአግባቡ እስከ መጨረሻው በመሳተፍ ከሌሎች ተወዳድሮ የተሻለ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡

## አንቀጽ 36 <u>በፀረ ሙስና ትግል ጉልህ አስተዋጽኦ ያደረገ ግለሰብ</u>

1. በራስ ተነሳሽነት የፀረ-ሙስና ትግሉን የሚያጐለብት ተግባር መፈጸም የሚለካው ግለሰቡ በራስ ተነሳሽነት በሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ዙሪያ በሰጠው ጥቆማ /መረጃ፣ ባስተላለፋቸው የሥነ-ጥበብና ኪነ-ጥበብ ሥራዎች/መዝሙር፣ድራማ፣ ግጥም፣ ሥነ-ጽሑፍ፣ ሥዕል ወዘተ/ተወዳድሮ ከሌሎች የተሻለ ሆኖ ሲገኝ ሲሆን የሚከተለውን መሥፈርት የሚያሟላ ነው፡፡

**ሀ/ለጥቆማ**

| ተ.ቁ | መስፈርት | ክብደት በመቶኛ | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | የጥቆማ ብዛት | 30 | |
| 2 | የማስረጃዎች ውጤታማነት | 30 | |
| 3 | የወንጀሎቹ ክብደት | 30 | |
| 4 | የግለሰቡ ሌሎች ተሳትፎዎች | 10 | |

ለ/ ለፈጠራ ስራ

| ተ.ቁ | መስፈርት | ክብደት በመቶኛ | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | የሥነ-ጥበብ /ኪነ-ጥበብ ሥራ ብዛት | 30 | |
| 2 | የሥነ-ጥበብ /ኪነ-ጥበብ ሥራ ይዘት | 30 | |
| 3 | የሥነ-ጥበብ /ኪነ-ጥበብ ወጥነት | 30 | |
| 4 | የግለሰቡ ሌሎች ተሳትፎዎች | 10 | |

2. አንድ ግለሰብ ያበረከተው አስተዋጽኦ የሚለካው ግለሰቡ የሰጠው ጥቆማና ማስረጃ በራሱ ወይም ከሌሎች መረጃዎች ጋር ተዳምሮ ክስ በተመሰረተበት ጉዳይ ላይ በፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ማሰጠት ሲችል ሆኖ፡-
   - ሀ/ ያቀረባቸው የሙስና ወንጀል ጥቆማዎች ብዛት ከሌሎች ተመሳሳይ ጠቋሚዎች ጋር ተወዳድሮ በልጦ ሲገኝ፣
   - ለ/ ያቀረባቸው የሙስና ወንጀል ማስረጃዎች ውጤታማነት ከሌሎች ተመሳሳይ ማስረጃ አቅራቢዎች ጋር ተወዳድሮ በልጦ ሲገኝ፣
   - ሐ/ የጠቆማቸው የሙስና ወንጀሎች ክብደት ከሌሎች ተመሳሳይ ጠቋሚዎች ጋር ተወዳድሮ በልጦ ሲገኝ፣
3. አንድ ግለሰብ ያበረከተው የፈጠራ ሥራ የሚለካው ሥራው ለፀረ-ሙስና ትግሉ የሚያኖረው አስተዋጽኦ ከሌሎች ጋር ተወዳድሮ በልጦ ሲገኝ ሆኖ፡-
   - ሀ/ ሥነ-ምግባርና ሙስናን አስመልክቶ ያዘጋጀው የሥነ-ጥበብ /ኪነ-ጥበብ ሥራ ብዛት ከሌሎች ጋር ተወዳድሮ በልጦ ሲገኝ፣
   - ለ/ ሥነ-ምግባርና ሙስናን አስመልክቶ ያዘጋጀው የሥነ-ጥበብ /ኪነ-ጥበብ ሥራ ይዘት ከሌሎች ጋር ተወዳድሮ በልጦ ሲገኝ፣
   - ሐ/ ያዘጋጀው የሥነ ጥበብ /ኪነ-ጥበብ ሥራ ወጥነት ከሌሎች ጋር ተወዳድሮ በልጦ ሲገኝ ነው፡፡
4. ማበረታቻው በግልጽ ወይም በዕቡዕ ሊሰጥ ይችላል፣
5. ለግለሰቦች ማበረታቻ ወይም እውቅናው በግልጽ ለመስጠት የጠቋሚዎቹ ስምምነት በኮሚቴ ተጠይቆ ይወሰናል፣
6. ለተቋማት/ለአካላት/ በግልጽ እውቅና ይሰጣል፣

## አንቀጽ 37 <u>ለልዩ ልዩ አካላት የሚሰጡ የዕውቅና ዓይነቶች</u>

1. አንደኛ ለወጣ ተቋም ወይም ግለሰብ ያደረገውን አስተዋጽኦ የሚገልጽ በጥምረቱ የተፈረመ 1ኛ ደረጃ ሠርተፊኬት፣
2. ሁለተኛ ለወጣ ተቋም ወይም ግለሰብ ያደረገውን አስተዋጽኦ የሚገልጽ በጥምረቱ የተፈረመ 2ኛ ደረጃ ሠርተፊኬት፣
3. ሶስተኛ ለወጣው ተቋም ወይም ግለሰብ በጥምረቱ የተፈረመ የምስጋና ደብዳቤ ይሆናል፡፡
4. ጥምረቱ እንደሁኔታው ከሠርተፊኬቱ በተጨማሪ አነስተኛ የገንዘብ ወይም የማቴሪያል ሽልማት ሊሰጥ ይችላል፡፡
5. ከሠርተፊኬት በተጨማሪ የገንዘብ ወይም የማቴሪያል ሽልማት የሚኖር ከሆነ ጥምረቱ አስቀድሞ ይህንኑ ለተወዳዳሪ አካላት ያሳውቃል፡፡

## አንቀጽ 38 <u>የማበረታቻ ዕውቅና ኘሮግራም አፈፃጸም ወጪ</u>

1. የእውቅና መስጫ ኘሮግራሙ የሚመለከታቸው አካላት በሚገኙበት ሥነ-ሥርዓት ይካሄዳል፣
2. የእውቅና አሰጣጡ ሥነ-ስርዓት የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኝ ይደረጋል፣
3. ዕውቅና ለመስጠት፣ የገንዘብ ወይም የማቴሪያል ሽልማት ለመስጠት የሚደረገው ኘሮግራም አፈፃጸም ወጪ በጥምረቱ ከሚመደብ በጀት የሚሸፈን ይሆናል፣

## አንቀጽ 39 <u>ዕውቅና የሚያገኙ አካላትን/ግለሰቦችን የሚለይ ኮሚቴ ስለመሰየም</u>

1. ዕውቅና የሚሰጣቸውን አካላት/ግለሰቦች መርጦ የሚለይ ኮሚቴ በሴክሬታሪያቱ አቅራቢነት በጥምረቱ ሰብሳቢና በሥራ አስፈፃሚ ተመርጦ ይሰየማል፣
2. የኮሚቴው አባላት ቁጥር ከአምስት መብለጥ የለበትም፣
3. የኮሚቴዉ ስብጥር ከመንግስት ተቋማት፣ ከሲቪክ ማህበራት፣ ከብዙሃን መገናኛና ከግሉ ሴክተር ይሆናል፣
4. ከመንግስት ተቋማት ሁለት ሆነው አንዱ ከኮሚሽኑ ይሆናል፣
5. ከሲቪክ ማህበራት፣ ከብዙሃን መገናኛና ከግሉ ሴክተር አንድ አንድ ይሆናል፣

## አንቀጽ 40 <u>የኮሚቴው አቋም</u>

1. በጥምረቱ ጠቅላላ ጉባኤና ሥራ አስፈፃሚ የሚወከል --------------------------- ሰብሳቢ
2. የጥምረቱ ምክትል ሰብሳቢ ወይም ከሌሎች አካላት --------------------------- አባል
3. የጥምረቱ ሁለት የሥራ አስፈፃሚ አባላት ወይም ከሌሎች አካላት------------- አባል
4. ከክልሉ የስቀነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሚወከል ወይም በየደረጃው አስተዳደር /ከንቲባ ጽ/ቤት የተቋቁመ የሥነ-ምግባር ኦፊሰር-----------ፀሐፊ ይሆናል፡፡
5. ለእውቅና ከሚመረጡት አካላት ውስጥ የኮሚቴው አባል የሆነ ግለሰብ ካለበት እሱ የሰጠው ጥቆማና ማስረጃ ወይም ያበረከተው የፈጠራ ስራ በሚለካበት ጊዜ ራሱን እንዲያገል ይደረጋል፡፡

## አንቀጽ 41 <u>የምዘና ሂደት</u>

1. ዕውቅና የሚያገኙ አካላት /ግለሰቦች ምዘና የሚከናወነው በመራጭ ኮሚቴው አማካኝነት ይሆናል፣
2. የመራጭ ኮሚቴው ምዘናውን የሚያካሄደው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 35 እና 36/ሀ እና ለ የተዘረዘሩትን መሥፈርቶች መሠረት በማድረግ በሚገኝ ውጤት ይሆናል፣
3. በውድድሩ መስፈርት በሚገኝ ውጤት ሁለት እና ከሁለት በላይ ተቋማት ወይም ግለሰቦች እኩል ነጥብ ካገኙ ሁሉም አንድ አይነት ዕውቅና ያገኛሉ፣

## አንቀጽ 42 <u>የኮሚቴው ተግባርና ሃላፊነት</u>

1. የሚቀርቡትን መረጃዎች ትክክለኛነት ያረጋግጣል፡፡
2. በተገኘው መረጃ መሠረት ዕጩዎቹን አወዳድሮ ይመርጣል፡፡
3. በምርጫው ሂደት የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በመቀበል ያስተናግዳል፣ በሚገኙ መረጃዎች መሠረት አስፈላጊ ማጣራትና ማስተካከያ ያደርጋል፡፡
4. የምርጫውን ውጤት ለጥምረቱ ጠቅላላ ጉባኤ ሰብሳቢ በማቅረብ ያስፀድቃል፡፡

**አንቀጽ 43 <u>የመረጃ ምንጮች</u>**

1. የሙስና ወንጀልና ብልሹ አሰራር መከላከል ዋና ሥራ ሂደት
2. የሙስና ወንጀል መመርመርና መክሰስ ዋና ሥራ ሂደት
3. የጥምረቱ ሴክሬታሪያት
4. በየደረጃው የተመሠረቱ ጥምረቶች ሥራ አስፈፃሚ
5. በየተቋሙና በየአስተዳደር እርከኑ የተቋቋሙ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኦፊሰሮች
6. እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች የኮሚሽኑ የሥራ ሂደቶችና አስተማማኝ የሆኑ ምንጮች
7. የየጥምረቱ አባል ተቋማት ናቸው

**አንቀጽ 44 <u>ዕውቅና የሚሰጥበት ጊዜ</u>**

የማበረታቻ ዕውቅና የሚሰጠው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 45 <u>ዕውቅና የሚያገኙትን ስለ ማሳወቅ</u>**

ጥምረቱ ዕውቅና እንዲሰጣቸው በኮሚቴው የተመረጡ አካላትና ግለሰቦች በጥምረቱ ሰብሳቢና በሥራ አስፈፃሚ ከጸደቀ በኋላ ለሥነ-ሥርዓቱ ተዘጋጅተው እንዲመጡ ከዕለቱ አሰቀድሞ ያሳውቃል፡፡

**ክፍል ሰባት**

**ስለጥምረቱ የፋይናንስ አስተዳደር**

**አንቀጽ 46 <u>ስለ ጥምረቱ በጀት</u>**

1. ጥምረቱ ለሚያከናውናቸው ተግባራት ወጪ መሸፈኛ በጀት በህጋዊ ደረሰኝ ይሰበስባል
2. የተሰበሰበው ገቢ በዚህ መመሪያ መሠረት የወጪ ትዕዛዝ ሊሰጥ በሚችል ሰው ወይም አካል ሲፈቀድ ብቻ ወጪ ይደረጋል፡፡
3. የጥምረቱ ገቢና ወጪ በየዓመቱ ኦዲት ይደረጋል፡፡

## አንቀጽ 47 <u>የጥምረቱ የፋይናንስ ምንጭ</u>

1. <u>ለክልሉ ፀረ-ሙስና ጥምረት</u>

   ሀ· አባላት የራሳቸውን ወጪ እንዲሸፍኑ በማድረግ፣

   ለ· ከለጋሾች በሚገኝ ድጋፍ፣

   ሐ· ከገቢ ማሰባሰቢያ ኘሮግራም እና

   መ· የክልሉ መንግሥት ለሴክሬያሪያቱ በሚመድበው በጀት ይሸፈናል፣

2. <u>በየደረጃው ለተቋቋመው ጥምረት</u>

የየጥምረቱ ሥራ አስፈፃሚ ለጥምረቱ ሥራ ማስኬጃ የሚሆነውን በጀት ከየት ከየት መሰብሰብ እንዳለበት ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 48 <u>በጀት ዝግጅትና አቀራረብ</u>

ለጥምረቱ ተግባራት ማከናወኛ የበጀት ግምት ከጥምረቱ ዕቅድ ጋር በሴክሬታሪያቱ ወይም በየደረጃው በተቋቋመው የሥነ-ምግባር ኦፊሰር ተዘጋጅቶ ለሥራ አስፈፃሚ ቀርቦ ይጸድቃል፡፡

## አንቀፅ 49 <u>ክፍያና ወጪ</u>

1. በጥምረቱ የተሰበሰበው ገቢ ለጥምረቱ ሥራ ማከናወኛ ብቻ ወጪ ይደረጋል፣
2. ለጥምረቱ ሥራዎች ከከተማቸው ውጪ ለሚንቀሳቀሱ ባለሙያዎችና ጥምረቱ በሚጠራቸው ስብሰባዎች ለሚሳተፉ ሰዎች በመንግስት ፋይናንስ ደንብ መሠረት የውሎ አበል ይከፈላል፡፡
3. የጥምረቱ ወጪዎች በጥምረቱ ሥራ አስፈፃሚ ሰብሳቢ ፊርማ ወይም እርሱ በፅሑፍ ውክልና በሰጠው ሰው ፊርማ ይፈጸማሉ፡፡
4. የጥምረቱ የፋይናንስ አስተዳደር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር መሠረት ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 50 <u>መዝገብ፣የገቢና ወጪ ደረሰኝ</u>

1. የሥራ አስፈፃሚው ከወሰነው ምንጮች የሚሰበሰበውን የጥምረቱን ገቢ ሴክሬታሪያቱ በደረሰኝ ይቀበላል ወይም ይሰበስባል፡፡

2. ሴክሬታሪያቱ የሥራ አስፈፃሚው ከወሰነው ምንጭ ወይም ምንጮች የጥምረቱ ገቢ የሚሰበሰብበት እና በህጋዊ መንገድ ወጪ የሚደረግበት ደረሰኞች አሳትሞ በሥራ ላይ ያውላል፡፡
3. ሥራ አስፈፃሚው ለጥምረቱ የተለየ የባንክ ሂሳብ እንዲከፈትና ሂሳቡ በራሱ ቼክ እንዲንቀሳቀስ ያደርጋል፡፡
4. ሴክሬታሪያቱ የመንግስት የፋይናንስ አስተዳደር በሚያዘው መሠረት የጥምረቱን ገቢና ወጪ የሚመዘግብባቸው መዛግብት ይኖሩታል፣

## አንቀጽ 51 <u>ኦዲትና ሪፖርት</u>

1. ሴክሬታሪያቱ እና በየደረጃው የተመሰረተው ጥምረት ለጥምረቱ ሥራ ተብሎ የተመደበ በጀትን በሚመለከት የተሟላ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡
2. የሂሳብ መዛግብቱ በየዓመቱ በህጋዊ ኦዲተር ኦዲት ይደረጋል፡፡
3. የመንግስት የበጀት ዓመት የጥምረቱ የበጀት ዓመት ሆኖ ያገለግላል፡፡
4. ኦዲት የተደረገው ሂሳብ የጥምረቱ ሥራ አስፈፃሚ አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጐ ለጥምረቱ ጠቅላላ ጉባዔ ይቀርባል፡፡
5. የጥምረቱ ጠቅላላ ጉባኤ በቀረበለት የኦዲት ሪፖርት ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ይሰጣል

## አንቀፅ 52 <u>የጥምረቱ የፋይናንስ አስተዳደር</u>

1. የጥምረቱ ሥራ አስፈፃሚ የጥምረቱን ፋይናንስ የሚያስተዳድሩ ባለሙያዎችን በክልል ደረጃ ከሴክሬታሪያቱ የሚመደብ ሲሆን በዞን፣ በልዩ ወረዳ፣ በወረዳና በከተማ አስተዳደር ደረጃ ከፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ ወይም ጽ/ቤት ይመደባል፡፡

## አንቀፅ 53 <u>የባለሙያዎች ሥራና ኃላፊነት</u>

የጥምረቱን ፋይናንስ የሚያስተዳድሩ ባለሙያዎች ሥራና ኃላፊነት በፋይናንስ ሴክተር ለሚሰሩ የፋይናንስ ባለሙያዎች የተሰጠ ሥራና ኃላፊነት ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ስምንት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

### አንቀፅ 54 <u>ተፈፃሚነት ስለሌላቸው መመሪያዎችና አሠራሮች</u>

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሌሎች መመሪያዎች ወይም አሠራሮች በዚህ መመሪያ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

### አንቀፅ 55 <u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>

የክልሉ የፀረ-ሙስና ጥምረት ሥራ አስፈፃሚ  አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው ጊዜ ይህን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

### አንቀፅ 56 <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከመስከረም 04 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

???? ???

**የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት**

**የፀረ-ሙስና ጥምረት ሰብሳቢ**